የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43825

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- የህፃን ኮከቤ ተፈሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ፀሐይ በየነ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- 1. አቶ አያሌው ካሳዬ - አልቀረቡም

2. አቶ ጣእመ ካሳዬ - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በሞግዚታቻው አማካኝነት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው የአመልካች እናት ንብረት ለማስተዳደር እንጂ ለመሸጥ ስልጣን ሳይኖራቸው ለአመልካች ከአባታቸው በውርስ የሚተላለፍላቸውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና ሁለተኛ ተጠሪም ወኪል ነኝ በማለት ቤቱን ይዘው ስለሚገኙ የሽያጩ ውል ፈርሶ ወደነበርበት እንዲመልሱ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክሱ ለተጠሪዎች ደርሷቸው በሰጡት መልስ ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም ክሱም በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም የሚለውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተከናወነ በመሆኑ ረቂቅ እንጂ በህግ ፊት የሚፀና ውል ስላልሆነ ውል በሌለበት ሁኔታ የውል ይፍረስልን ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም፣የይርጋ መቃወሚያም ሊቀርብበት አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ውሳኔን አጽቶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት የውል አፃፃፍ ፎርም አለመከተል በተዋዋይ ወገን ወይም በማናቸውም ያገባኛል ባይ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የሚታይ ነው ወይስ ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ሊያየው ይችላል? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡ መርምሯል፡፡

አመልካች በሞግዚታቸው አማካኝነት ያቀረቡት ክስ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስና ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ይህ ውል ስለመደረጉ አምነው ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤት የቤት ሽያጩ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም ፍ/ቤቱ ያልተደረገ በመሆኑ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ውል የለም በማለት ወስኗል፡፡ በእርግጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በፁሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም በፍ/ቤት ካልተደረገ ውጤት የሌለው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህን በሕጉ የተመለከተው የአፃፃፍ ስርአትን አለመከተል የሚያስከተለው ውጤት ምን እንደሆነ ደግሞ በዚሁ ሕግ ቁጥር 1808/2/ ስር ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የአፃፃፍ ስርአት ያላሟላ ውል የሚፈርሰው ከተዋዋዮቹ በአንዱ ወይም ማናቸውም ጥቅም ያለው ሰው ሲጠየቅ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም አንድ የአፃፃፍ ስርአትን ያላሟላ ውል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈርስር ጥያቄ አስካልቀረበበት ድረስ ከጅምሩ ፈራሽ ነው ሊባል እንደማይችል ያስገነዝበናል፡፡ ውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምክንያት እንዲፈርስ ጥያቄ እስካልቀረበ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት የአፃፃፍ ስርዓቱን ምክንያት በማድረግ ውሉን ከጅምሩ ውድቅ ሊያደርግ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤት በውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምንም አይነት ክርክር ሊቀርብበት አይችልም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14336 በሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59734 ኅዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን እና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ